# የቤተክርስቲያን ታሪክ መግቢያ

የቤተክርስቲያን ታሪክ መግቢያ

# ማውጫ


የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መግቢያ ...... 216
ሀ. የቤተክርስቲያን ታሪክ ትርጉም ...... 216
ለ. የቤተክርስቲያን ታሪክ ጥቅም ...... 217
ሐ. የቤተክርስቲያን ታሪክ ጥናት ምንጮች ...... 217
መ. የቤተክርስቲያን ዘይቤያዊ ፍቺ ...... 217
ሠ. የቤተክርስቲያን ሰድሚ ...... 219

**ክፍል አንድ**

- ☞ ዓለመ መላእክት ...... 220
- ☞ ክፍል ሁለት ...... 220
- ☞ በብሉይ ኪዳን የነበሩ ደጋግ አባቶች ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ...... 220

**ምዕራፍ አንድ**

- ☞ ዘመነ አበው ...... 220
- ☞ ከአዳም እስከ ዮሴፍ ...... 220

**ምዕራፍ ሁለት**

- ☞ ዘመነ መሳፍንት ...... 227
- ☞ ከሙሴ እስከ ሳሙኤል ...... 227

**ምዕራፍ ሦስት**

- ☞ ዘመነ ነገሥት ...... 233
- ☞ ከሳኦል እስከ ሮብአም ...... 233
- ☞ ማጠቃለያ ...... 235

**ምዕራፍ አራት**

- ☞ ዘመነ ነቢያት/ካህናት/ ...... 238

**ክፍል ሦስት**

- ☞ አማናዊት ቤተክርስቲያን ...... 248

**ምዕራፍ ሁለት**

- ☞ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ የነበረው የዓለም ሁኔታ ...... 248
- ☞ ፈሪሳውያን፣ ሰዱቃውያን እና ኤሴዎች/ኤስያውያን/ ...... 248
- ☞ የመሲህ መምጣት ተስፋ ...... 248
- ☞ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የዘመነ ሥጋዌ ጉዞ ...... 240
- ☞ የክርስቶስ ጥምቀት ...... 242
- ☞ የክርስቶስ ጾም ...... 243
- ☞ የሐዋርያት መጠራት ...... 243
- ☞ የክርስቶስ ትምህርት ...... 246
- ☞ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማኅበራዊ ኑሮ ...... 247
- ☞ የሐሙስ እራት ...... 248
- ☞ የጌታችን መያዝ ...... 248
- ☞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ...... 249
- ☞ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መቀበር ...... 250
- ☞ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ...... 250
- ☞ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት ...... 251
- ☞ ጽርሐ ጽዮን ...... 252

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# የቤተክርስቲያን ታሪክ መግቢያ

እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- *«በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ፤ በእርስዋም ላይ ሂዱ ለነፍሳችሁም ዕረፍትን ታገኛላችሁ፡፡»*

ኤር. 6÷16

ትርጉም፡- ቤተክርስቲያን

- **ቤት** ፡- ማደሪያ መኖሪያ ከድንጋይ ከጨቃ የተሠራ
- **ክርስቲያን** ፡- የክርስቶስ ተከታይ፣ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር፣ የክርስቶስ ወገን በስሙ ያመነ የተጠመቀ (ደስታ ተ/ወልድ መዝገበ ቃላት)
- **ቤተክርስቲያን**፡- የክርስቶስ ወገኖች ለጸሎትና ለስግደት ለቁርባን የሚሰበሰቡባት ታቦትና መስቀል ሥዕል ያለባት የክርስቲያን ቤት ባለ ሦስት ክፍል (ደስታ ተ/ወልድ መዝገበ ቃላት)
- ***ታሪክ***፡- ዜና ያለፈ ነገር በቃል በመጽሐፍ ሲያያዝ የመጣ

## *ሀ. <u>የቤተክርስቲያን ታሪክ ትርጉም</u>፡-*

የቤተክርስቲያን ታሪክ ማለት የክርስትና እምነት ታሪክ ማለት ነው፡፡ በቤተክርስቲያን ታሪክ ትምህርታችን የክርስትና እምነት የአምላክ መገለጥ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዘመንና በቦታ የተደረገ ስለሆነ መቼ? እንዴት? እንደሆነ የምናውቅበትና በጉዞው ሁሉ የገጠሙትን ችግሮችና ምቾቶች የምንማርበት ነው፡

- የቤተክርስቲያን ታሪክ፡- ቤተክርስቲያን በክርስቶስ መሠረትነት ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዘመናችን ድረስ ያለውን ታሪኳን እንደምን እንደተመሠረተች፤ ዓለም ህዝብ እንዴት እንደተቀበላት፤ በየጊዜው ከአባላቷና ከተቃዋሚዎቿ የተሰነዘሩባትን የኑፋቄ ትምህርቶችና ስደቶች በጸና ሃይማኖት በመቋቋም (በመጋደል) እንደምን እንዳሳለፈቻቸው፤ የእግዚያብሔርን ቃል እንዴት እንዳስፋፋች፤ ይህም ብቻ ሳይሆን በጉዞው ሁሉ የገጠሙትን ችግሮችና ምቾቶች የምንማርበት ነው፡፡
- የቤተክርስቲያን ታሪክ የሚያጠና ተማሪ ከቤተልሔም ዋሻ እስከ ቀራንዮ ከካታካምቦ (ግበበ ምድር) ሕይወት ጀምሮ እስከ አለንበት ጊዜ ድረስ ያለውን ሁኔታ እያወዳደረ ያጠናል፡፡ በዚህም የጥናት ጊዜው ያለፈውን ያውቃል፤ ያለበትንም ሁኔታ ያስተውላል ፤ ለሚመጣውም ትውልድ ማሳደጊያ ቅርስ በማስታወሻ ቋጥሮ ያስቀምጣል፡፡

## ለ. የቤተክርስቲያን ታሪክ ጥቅም:-

1. የቤተክርስቲያን ታሪክ ከዓለም ታሪክ አንዱን ክፍል ይዞ ስለሚገኝ የሕዝቦችን የሥልጣኔ እርምጃና ታሪክ ለማጥናት ለሚፈልግ ሰው ጠቃሚ መረጃ ይሰጣል::
2. አንድ ምዕመን የቤተክርስቲያንን ታሪክ ለማጥናት በሚፈልግበት ጊዜ:-
   - የእምነቱን ታሪክ ለማወቅ፣
   - አባቶች በየጊዜው ስላስተማሩት የትምህርት፣ የሕዝብ ፀባይ እንዴትእንደተሻሻለ ለማወቅና ራስን ለማነጽ፣
   - የቤተክርስቲያንን ከፍተኛነትና ጠቃሚነት ለመገንዘብና ራስንም በእምነት ለማጽናት ከፍተኛ ጥቅም አለው::

## ሐ. የቤተክርስቲያን ታሪክ ጥናት ምንጮች:-

የቤተክርስቲያንን ታሪክ በዝርዝር ለማጥናት ለሚፈልግ ሰው:-

1. ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን /መጽሐፍ ቅዱስ/ እና የትርጓሜ መጻሕፍት፣
2. የቤተክርስቲያን ታሪክ አባቶች የጻፏቸው መጻሕፍት /በየጊዜው በተደረጉ ጉባዔ ዎች የተወሰኑትንና ነገሥታት ስለቤተክርስቲያን የደነገጓቸው ህጎች፣
3. ታሪኩ በተፈጸመበት ቦታ ተገኝተውና ታሪኩ በተፈጸመበት ዘመን የኖሩ የቤተክርስቲያንና የውጭ ታሪክ ፀሐፊዎች የጻፏቸው መጻሕፍት፣
4. በየጊዜው የተገኙ የክርስቲያኖች መቃብራት፣ መቅደሶች፣ሥዕሎች፣ ገንዘቦች ጽሑፎችና እነዚህን የመሳሰሉት ቅርሶች /ለማገናዘቢያነት የሚ ረዱ/፣
5. የቤተክርስቲያን ትውፊታዊ መረጃዎች ያስፈልጉታል::

## መ. የቤተክርስቲያን ዘይቤያዊ ፍቺ:-

በሰዋስው አወጣጥ "ቤተክርስቲያን" የሚለው ቃል ሦስት ትርጉም አለው::

1. "ቤተክርስቲያን" የግእዝ ቃል ሲሆን በአማርኛም እንጠቀምበታለን:: ፍቺውም ህፃኑ፣ ሽማግሌው፣ ወንዱ፣ ሴቱ፣ የተማረው፣ ያልተማረው አንድ ላይ ተ ሰባስቦ ጸሎት የሚያደርስበትን የጌታችን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም የሚፈተ ትበት ቅዱስ ቦታ /ሕንፃ ቤተክርስቲያንን/ ያመለክታል:: የሐዋ. ሥራ 20÷28፣ 1ኛ ጢሞ.3÷15፣ 1ኛ ነገ.9÷3::

2. ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ የዓለም መድኃኒት መሆኑን የሚያምኑ፤በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነው የተጠመቁ ሰዎች ሁሉ ቤተክርስቲያን ይባላሉ:: የያዕቆብ /የእስራኤል/ ወገን የሆኑ በሙሉ ቤተእስራኤል እንደሚባሉ ሁሉ በክርስትና የክርስቶስ የሆኑ የክርስቲያን ወገኖችም ቤተክርስቶስ፣ ቤተክርስቲያን ይባላሉ:: የሐዋ.ሥራ 5÷11፣ የሐዋ.ሥራ 12÷1፣ 1ኛቆሮ.3÷16፣ 2ኛቆሮ.6÷16፣ ዮሐ.14÷23፣ የሐዋ.ሥራ 9÷3::

3. የክርስቲያኖች ማኅበር፣ የክርስቲያኖች ጉባዔ፣ የክርስቲያኖች ስብስብ /አንድነት/ ቤተክርስቲያን ይባላል:: "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን" እንዲል:: ሮሜ.16÷1፣ 1ኛ ጴጥ.5÷13::

## የቤተክርስቲያን ቅጽል ስሞች

1. **ኦርቶዶክስ ተዋህዶ**፡- የቀናች የተዋህዶ እምነት ማለት ነው፡፡ / ይህንን ትምህርት በስፋት በካልዓይ ክፍል ያገኙታል፡፡
2. **ቤተክርስቲያን አንዲት ናት**፡- ቤተክርስቲያን በወርቅ፣ በአፈር፣ በከተማ፣ በገጠር፣ ከሀገር ውጭ ከሀገር ውስጥ ብትሠራ ክብሯ አንድ ነው፡፡ ምዕመናንም እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው ሃይማኖታቸውን ይመሰክሩባታል፡፡ የአንድ የክርስቶስ አካል ናት፡፡ ሮሜ 12÷4-5፣ 1ኛ ቆሮ. 12÷12-27 ኤፌ 4÷4-5
3. **ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት**፡- ክርስቶስ በቅዱስ ደሙ መሥርቷታል፡፡ አንፅቷታልና፣ ቀድሷታልና፡፡ ኤፌ.5÷26፣ የሐዋ. 20÷28 ቅድስና የባህሪው የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ናት፡፡ 1ኛ ቆሮ. 3÷10 በኃጢአት በክህደት ረክሰው የነበሩ በእምነት በንስሐ ወደሷ ገብተው ይቀደሳሉና:: 1ኛ ቆሮ 6፥9-11
4. **ቤተክርስቲያን ዓለም አቀፋዊት ናት** /የሁሉና በሁሉ ያለች ናት/፡- ቤተክርስቲያን በቦታ በዘርና በቋንቋ አትከፋፈልም አትወሰንም ወይም የእነገሌ ናት የእነገሌ አይደለችም አትባልም፡፡ ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው በክርስቶስ ደም ነው፡፡ ክርስቶስ የተሰቀለው ለዓለም ሁሉ ድኅነት ነው ክርስቶስ ለሁሉም ነው የሞተው፡፡ ገላ. 3÷25-28፣ ቆላ.3÷11፣ ማቴ. 28÷19

5. <u>ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት ናት</u>፡- ቤተክርስቲያን ሐዋርያዊት ናት የተባለችው በሐዋርያት ተመሥርታ፣ የሐዋርያትን እምነት፣ ትምህርትና ትውፊት ተቀብላ የምታስተምር ስለሆነች ሐዋርያዊት ትባላለች፡፡ 1ኛ ዮሐ. 1÷1-3፣ ማቴ. 10÷18፣ ሉቃ. 22÷30
   - የእስራኤል ዘሥጋ ታሪክ በአሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች እንደተጀመረ የእስራኤል ዘነፍስ የክርስቲያኖች እምነት ምስክሩ የሐዋርያት ትምህርት ነውና፡፡
   - እኚህ የተጠሩና የተመረጡ ቅዱሳን ሐዋርያት በዓይናቸው አይተውታል፣ በእጃቸው ዳሰውታል፣
   - ትምህርቱን በጆሮአቸው ሰምተውታል 1ኛ ዩሐ 1÷1-2 ፤ በእርሱ ተልከዋል ማቴ10÷1-4
   - ከትንሣኤውም በኋላ አይተውታል ዮሐ 21÷1 በስሙ ሐዋርያዊ ተአምራት ሲፈጽሙ ኖረዋል፡፡ ስለዚህ ሐዋርያት ስለ ክርስቶስና ስለቤተክርስቲያኑ የተናገሩት እውነት ነው፡፡ ቤተክርስቲያንም ሐዋርያዊት ናት እርሷም ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን ናት ኤፌ 2÷20፣ "በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል" እንዳለ
6. ቤተ ክርስቲያን በሰማይም በምድርም ያለች ናት፡- ቤተክርስቲያን በሰማይም በምድርም ያለች ናት ሲባል ምድራዊ ሥርዓት በሰማያዊ ሥርዓት የተሠራ ነው፡፡ 1ኛ ዜና 28÷19

## ሠ. <u>የቤተክርስቲያን ዕድሜ፡-</u>

አንዳንድ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ቤተክርስቲያን የሚለውን ቃል በምሥጢራዊ አፈታት ሲፈቱት፣ ቤተክርስቲያን ማለት እግዚአብሔር ከሰውና ከመላእክት ጋር ያለው ግንኙነት ነው ይላሉ:: በዚህም መሠረት የቤተክርስቲያንን ዕድሜ በሦስት ይከፍሉታል::

1. ሰው ከመፈጠሩ በፊት በዓለመ መላእክት የነበረች የቅዱሳን መላእክት አንድነት
2. በዘመነ ብሉይ የነበሩ ደጋግ አባቶች ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ግንኙነት
3. በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተመሠረተችውና በመንፈስ ቅዱስ የምትመራው አማናዊት ቤተክርስቲያን /የምዕመናን አንድነት/:: እሷም የፀጋና የጽድቅ ምንጭ ናት:: ኤፌ. 3÷9-11::እነዚህንም የቤተክርስቲያን ዕድሜዎች በዝርዝር ስንመለከታቸው:-

### <u>ጥያቄ፡-</u>

1. ቤተክርስቲያን ምንድናት?
2. ቤተክርስቲያን ለምን እንመጣለን?